# ለትምህርት ቤት ዕድሜ እና የበጋ መዋለ ሕጻናት

**ከትምህርት ቤት በፊት/በኋላ እና የበጋ መዋለ ሕጻናት**

ዕድሜያቸው ለትምህርት ቤት ለደረሱ ፕሮግራሞች ለልጆችና ለወጣቶች ‘ለመዋያ’ የሚያስችላቸው ከአደጋ የተጠበቀ እንዲሁም ጠቃሚ ማህበረሰባዊ ልምዶችን እንዲማሩና እንዲያዳብሩ መዋያ ቦታ ያቀርባል።


- በዕድሜ ለትምህርት ቤት ለደረሱ ልጆች ምን ዓይነት አገልግሎት ይቀርባል?
- ከትምህርት ቤት በፊት ወይም በኋላ የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት የማገኘው የት ነው?
- ምን መፈለግ አለብኝ?
- መጋገዣስ?
- የወረዳ ትምህርት ቤት ጽ/ቤት መገናኛዎች
- ልጄ ብቻውን/ብቻዋን እቤት ለቀመጥ ዝግጁ ነው/ነች?
- በተጨማሪም ይመልከቱ - ለተጨማሪ አገልግሎቶች መረጃ


**በዕድሜ ለትምህርት ቤት ለደረሱ ልጆች ምን ዓይነት አገልግሎት ይቀርባል?**

በዕድሜ ለትምህርት ቤት ለደረሱ ልጆች የሚቀርቡ ሁለት ዓይነት መሠረታዊ የመዋለ ሕጻናት አገልግሎቶች አሉ፤ የሥራ ፈቃድ ያላቸውና ከሥራ ፈቃድ ነፃ የሆኑ መዋለ ሕጻናት ፕሮግራሞች። የሥራ ፈቃድ ያላቸው የመዋለ ሕጻናት ፕሮግራሞች ከአደጋ መጠበቅን፣ የአዋቂዎች-ልጆች ቁጥር ተመዛዛይነትን፣ ወዘተ አስመልክቶ በዲኤስኤችኤስ የወጣውን መመሪያዎች ይከተላሉ። ልጁ/ጅቷ እዚያ በሚውልበት/በምትውልበት ጊዜ ለደህንነታቸው ፕሮግራሙ ኃላፊ ነው። ፕሮግራሙ ለልጆቹ የታወቀ ግብና ተግባራት አሉት። ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ለፕሮግራሙ ማስመዝገብ አለባቸው ደግሞም ልጆች ወጥተው መሄድ የሚችሉት ፈቃድ ከተሰጠው አዋቂ ሰው ጋር ብቻ ነው። ደግሞም እነዚህ ፕሮግራሞች ለቀረበው የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት የዲኤስኤችኤስ ክፍያዎችን ይቀበላሉ።

- ስለ ሥራ ፈቃድ
- የሥራ ፈቃድና አቤቱታዎች

የሥራ ፈቃድ ከማውጣት ነፃ የሆኑ ፕሮግራሞች በእያንዳንዱ ፕሮግራም የወጡትን አጠቃላይ “የቤት ውስጥ ደንቦችን” ይከተላሉ። በፕሮግራሙ ተካፋይ ለመሆን ልጆች መመዝገብ አያስፈልጋቸውም እናም እንደፈለጋቸው መምጣትና መሄድ ይችላሉ። ፕሮግራሙ ስለ ልጁ/ጅቷ ደህንነት ኃላፊነት አይወስድም። የፕሮግራሙ ተግባራት የሚዘጋጁት በየቀኑ ነው እናም የተወሰነ ግብ የላቸውም።

ከላይ

**ከትምህርት ቤት በፊት ወይም በኋላ የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት የማገኘው የት ነው?**

የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት ምንጭ መምሪያ አገልግሎት በልጅዎ ትምህርት ቤት አቅራቢያ የሚገኝ ከትምህር ቤት በፊት ወይም በኋላ የመዋያ ፕሮግራም ያላቸውን ባለሥራ ፈቃድ አገልግሎት አቅራቢዎች ማግኘት እንዲችሉ ይረዳዎታል። አገልግሎታችን ለልጅዎ የበጋ ጊዜ መዋለ ሕጻናት ፕሮግራም ማግኘት እንዲችሉ ይረዳዎታል። እንደ ዋይኤምሲኤ፣ ዋይደብልዩሲኤ፣ የወጣት ወንዶችና ልጃገረዶች ክበብና የመናፈሻና መዝናኛ ድርጅቶች የመሳሰሉት የማህበረተሰብ ፕሮግራሞች ዕድሜያቸው ለትምህር ቤት ለደረሱ የመዋያ አገልግሎትና የበጋ ጊዜ የውጭ መዝናኛ አገልግሎትን ይሰጣሉ። አንዳንድ ትምህርት ቤቶች እዚያው ቦታ ከሚሰጡ ፕሮግራሞች ጋር ከትምህርት ቤት በፊትና በኋላ አገልግሎቶችን ያቀርባሉ።

የእነዚህን ፕሮግራሞች ዝርዝር በሲያትል፣ ኬንትና ሬንተን ውስጥ በአብዛኞቹ ‘ኢንሸዬቲቭ እና ኦንላየን መረጃ ማስቀመጫ በኩል ማግኘት ይችላሉ።

- ዌብ ሳይት፣ http://www.ci.seattle.wa.us/~most/

ሲያትል ቻይልድና ኢስትሳይድ ፓረንት የመሰሉት የአካባቢ ጋዜጣዎችና መጽሔቶች ብዙውን ጊዜ የበጋ ፕሮግራሞችን ስም ዝርዝር ያወጣሉ።

ከላይ

**ምን መመልከት አለብኝ?**

ለእያንዳንዱ የዕድሜ ወይም ፍላጎት ምድብ የተለያዩ ቦታዎች ያሏቸውን የአገልግሎት ዝግጅቶች ይፈልጉ። ለምን ዓይነት ተግባራት ዕቅድ እንደወጣ ያጣሩ። በቤት ውስጥና ውጭ ተግባራት፣ በትልቅና በትንሽ ምድቦች ተግባራት፣ እና እንቅስቃሴ ባሉባቸውና ፀጥ ባሉ ቦታዎች መካከል ጥሩ ሚያዛናዊ የሆነ ሁኔታ እንዳለ ይመልከቱ። ልጅዎ በአገልሎቱ አቀራቢ የሥራ ባልደረባ በሚመሩ ተግባራትና በግል በሚመሩ ተግባራት መካከል መምረጥ መቻል አለበት/አለባት። ዕድሜያቸው ለትምህርት ቤት ለደረሱ የሚቀርቡ ፕሮግራሞች በናሽናል እስኩል ኤጅ አላያንስ ተቀባይነት ሊኖራቸው ይችላሉ።

- የናሽናል እስኩል ኤጅ ዌብ ሳይት
- ለመዋለ ሕጻናት አገልግሎት አቅራቢዎች ቃለ መጠይቅ ማድረጊያ ዝርዝር (አክሮባት)
- የኦንላየን መረጃ ማስቀመጫችንን ይመልከቱ

ከላይ

**መጋገዝስ?**

ዕደሚያቸው ለትምህርት ለደረሱ መዋለ ሕጻናት ላይ ከሚገጥሙት አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ዋነኛው ልጅዎ ለፕሮግራሙ ወደ ትምህርት ቤት እንዲሁም ተመልሶ ወደ ፕሮግራሙ እንዴት እንደሚመላለስ ነው። የወረዳ ትምህርት ቤት ጽ/ቤቶች በተወሰኑ አካባቢዎች ውስጥ ላሉ ትምህርት ቤቶች መጓጓዣ ያቀርባሉ እናም ብዙዎቹ ዕድሜያቸው ለትምህርት ለደረሱ የሚቀረቡ ፕሮግራሞች የትምህርት ቤቱን አውቶቡስ ሊጠቀሙ ይችላሉ። ደግሞም ጥቂት ፕሮግራሞች ራሳቸው መጓጓዣ ያቀርባሉ። የወረዳ ትምህርት ቤቶች ጽ/ቤት ወይም ፕሮግራሙ መጓጓዣውን ካላቀረቡ ለልጅዎ መጓጓዣውን ለማዘጋጀት ኃላፊ ይሆናሉ።

ከላይ

**ለእርስዎ ተጨማሪ መረጃ ሊሰጡዎ የሚችሉ የወረዳ የትምህርት ቤቶች መገናኛዎች እኚሁና።**

- ኦበርን ወረዳ ትምህርት ቤት ጽ/ቤት - www.auburn.wednet.edu
- ቤልቪው ወረዳ ትምህርት ቤት ጽ/ቤት - www.belnet.k12.wa.us
- ኢነምክላ ወረዳ ትምህርት ቤት ጽ/ቤት - www.enumclaw.wednet.edu
- ፌደራል ዌይ ወረዳ ትምህርት ቤት ጽ/ቤት - www.fwsd.wednet.edu
- ሃይላየን ወረዳ ትምህርት ቤት ጽ/ቤት - www.hsd401.org
- ኢሳኳ ወረዳ ትምህርት ቤት ጽ/ቤት - www.issaquah.wednet.edu
- ኬንት ወረዳ ትምህርት ቤት ጽ/ቤት - www.kent.wednet.edu
- ሌክ ዋሽንግተን ወረዳ ትምህርት ቤት ጽ/ቤት - www.lkwash.wednet.edu
- መርሰር አያላንድ ወረዳ ትምህርት ቤት ጽ/ቤት - www.misd.wednet.edu
- ኖርዝሾር ወረዳ ትምህርት ቤት ጽ/ቤት - www.nsd.org
- ሬንተን ወረዳ ትምህርት ቤት ጽ/ቤት - www.renton.wednet.edu
- ሪቨርቪው ወረዳ ትምህርት ቤት ጽ/ቤት - www.riverview.wednet.edu
- ሲያትል ወረዳ ትምህርት ቤት ጽ/ቤት - www.seattleschools.org
- ሾርላየን ወረዳ ትምህርት ቤት ጽ/ቤት - www.shorelineschools.org
- ስኖኳልሚ ወረዳ ትምህርት ቤት ጽ/ቤት - www.snoqualmie.wednet.edu
- ታሆማ ወረዳ ትምህርት ቤት ጽ/ቤት - www.tahoma.wednet.edu
- ተክዊላ ወረዳ ትምህርት ቤት ጽ/ቤት - www.tukwila.wednet.edu

ከላይ

**ልጀ ብቻውን/ብቻዋን እቤት ለቀመጥ ዝግጁ ነው/ነች?**

ልጅዎን ብቻውን/ዋን እቤት ለመተው የሚወስዱት ውሳኔ የግል ውሳኔ ሲሆን ለልጅዎ ባለዎት ዛሳብና ልምድ የተመሠረተ መሆን ይገባዋል። የዋሽንግተን ስቴት አንድ ልጅ በምን ያህል ዕድሜው/ዋ ብቻውን/ዋን እቤት መቀመጥ እንዳለበት/ባት የሚገልጹ ሕጎች ወይም ደንቦች የሉትም። በአጠቃላይ ከ10 ዓመት በታች የሆናቸው ልጆች ብቻቸውን መተው የለባቸውም፡ እንዲሁም ሕጻናትና ትንሽ ልጆች ለጥቂት ደቂቃም እኳ ቢሆን ብቻቸውን መተው የለባቸውም። ልጅዎን ብቻውን/ዋን እቤት ጥለው ከመሄድዎ በፊት እራስዎን ከሚይቁባቸው ጥያቄዎች ጥቂቹ እነኚሁና።

- ልጅዎ እቤት ብቻውን/ዋን ሲቀመጥ/ስትቀመጥ የፍርሐት ወይም የመረበሽ ስሜት አለው/ላት?
- ልጅዎ ተዛዝዎችዎንና ደንቦችዎን ይከተላል/ትከተላለች?
- ልጅዎ እውነቱን እንደሚነግርዎት/እንደምትነግርዎት ይተማመኑበታል/ባታል?
- ልጅዎ ባልታሰበ ወይም በድንገተኛ ጊዜ በዛቡ/ቧ ተረጋግቶ/ታ እንደሚቀመጥ/እንደምትቀመጥ እምነት ይጣልበታል/ባታል?
- ልጅዎ ሳይርበተበት/ሳትርበተበት 911 መደውል፡ ሙሉ ስምን (የእርስዎንም)፡ የመንገድ አድራሻና የስልክ ቁጥር መናገርና ስለደረሰው ሁኔታ ማብራራት ይችላል/ትችላለች?

ልጅዎን ለአጭር ጊዜ ያህል ትተው መሄድ በመጀመር ስጋትዎን ሊቀነሱ ይችሉ ይሆናል። ቀስ በቀስ እርስዎና ልጅዎ ሁኔታውን የምትለምዱት እንደሆነ ያረጋግጡ።

ከላይ

**በተጨማሪም ይመልከቱ**

- መድሐኒት ከመኖሪያ ቤት ርቀው ሳሉ
- የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት አቅራቢ መፈለጊያቸችን ይሞክሩ